በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የታክስ መረጃ አያያዝንና አስተዳደርን አስመልክቶ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ሕዳር 2006 ዓ.ም

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የባለስልጣኑ ተልዕኮ እና ራዕይ 1

የባለስልጣኑ ራዕይ 1

የባለስልጣኑ ተልዕኮ 2

የባለስልጣን መ/ቤቱ ዓላማ ስልጣን እና ተግባር 2

ዓላማ 2

የባለስልጣኑ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር 2

የባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል 3

ድርጅታዊ መዋቅር 3

የሰው ኃይል 4

የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ 4

የክዋኔ ኦዲቱ አላማ 4

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 5

የኦዲቱ አካባቢ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች 5

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት 6

የታክስ መረጃ አስተዳደር የስራ ሂደት ስዕላዊ መግለጫ 7

ክፍል ሁለት 8

ግኝቶች 8

I. የግብር መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና የአስተዳደር ስርዓት የተጣጣመ ወጥ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፡፡ 8

ዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አስተዳደር መኖሩን በተመለከተ፣- 8

የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር አሰጣጥን በተመለከተ 9

ግብር ከፋዮች የመክፈያ ጣቢያ ሲቀይሩ መረጃቸው የሚተላለፍ መሆኑን በተመለከተ 10

በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (በSIGTAS) እና በቅ/ፅ/ቤቶች የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ ተመሳሳይና የሚናበብ መሆኑን በተመለከተ 11

የግብር ከፋዮች የግዥ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ተጠናቅረው በመረጃ ቋት /Data Base/ በማእከል መያዛቸውን በተመለከተ 13

የግብር ከፋዮዎች ሀብትና ንብረት መረጃ ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ 14

የታክስ መረጃ አሰባሰብና አስተዳደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መዘጋጀቱን በተመለከተ 15

በፌዴራል፣ በክልል መንግስት እና በከተማ መስተዳደሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ መኖሩን በተመለከተ 16
የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆኑ የሚገባቸው ግብር ከፋዮችን በተመለከተ 17
የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌርን በተመለከተ 18
የሽያጭ መሳሪያዎች ጥገናን በተመለከተ 20
II መረጃን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረግ ቅንጅታዊ አሰራርና የድጋፍና ክትትል ሂደቱ ዉጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡፡ 23
የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች መረጃን በተገቢው መንገድ ስለመመዝገባቸው የሚያደረግውን ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ 23
ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች መረጃ አያያዝን በተመለከተ 24
ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ የሚረዱ መረጃዎች ተጠናቅረው መያዛቸውን እና ጥቅም ላይ መዋላቸውን በተመለከተ 25
የመረጃ አቅርቦት መስጫ ማዕከል መኖሩን በተመለከተ 27
ክፍል ሶስት 28
መደምደሚያዎች 28
ክፍል አራት 31
የማሻሻያ ሀሳቦች 31
አባሪ 1 35
የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች 35
አባሪ 2 37
የባለሥልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር 37
አባሪ 3 38
የሽያጭ መ/መ/መሳሪያ አቅራቢዎች ከሸጡት ውስጥ በአማካይ በዓመት ለጥገና የቀረቡ እና ተጠግነው የወጡትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ 38

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በኢትዮጵያ የቀረጥና የግብር አሰባሰብ ረጅም ታሪክ ያለውና ወደ ውጭ ለሚላኩና ከሀገር ለሚወጡ መሳሪያዎች እንደየመጠናቸው በዓይነት ታክስና ቀረጥ እንዲከፈል ተደንግጎ ነበር፡፡ በመቀጠል በ1692 ዓ.ም.የቀረጥ አከፋፈል ሥርዓት ደንብ በማበጀት የቀረጥ መቅረጫ ቦታዎች፣ የቀረጡ መጠን እና ቀረጥ የማይመለከታቸውን በመለየት አፄ እያሱ አዋጅ አውጀው ነበር፡፡ ከዚያም በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በንጉስ ምስል የተሰራ ገንዘብ ሲታተም የግብርና የጉምሩክ ክፍል በ1901 ዓ.ም.ተቋቋመ፡፡ የነበረው የጉምሩክ አሠራር አንዳንድ መሻሻል እየተደረገበት እስከ ጠላት ወረራ ድረስ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ከጠላት ወረራ በኃላ ጉምሩክ በአዲስ መልክ በ1935 ተቋቋሞ ሥራውን የጀመረ ሲሆን ሥራውንም የሚያግዙ የተለያዩ አዋጆችና ደንቦች ታውጀዋል፡፡
2. ከ1966 አብዮት በኋላ በነሐሴ 1967 ዓ.ም. የጉምሩክ ቀረጥና ኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር በመባል በአዲስ መልክ ተዋቀረ፡፡ የአለም ጉምሩኮች ሕብረት ምክር ቤት ያዘጋጀውን የንግድ ሸቀጦችን በተሰሩበት ንጥረ ነገር እና በአገልግሎታቸው የሚመድበው የታሪፍ መጽሐፍ ከነሐሴ 1967 ዓ.ም.ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ፡፡
3. የጉምሩክ ቀረጥና ኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ይባል የነበረው በ1989 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 60/1989 የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በመባል ተጠሪነቱ ለገቢዎች ቦርድ እንዲሆን ተደንግጎ እንደገና ተቋቋመ፡፡ ከዚያም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለገቢዎች ሚንስቴር እንዲሆን ተደረገ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተዋህደው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን" በመባል ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደንግጎ ተቋቋመ፡፡

የባለስልጣኑ ተልዕኮ እና ራዕይ

የባለስልጣኑ ራዕይ

4. "በ2020 በአፍሪካ ግንባር ቀደም የሆነ ዘመናዊ እና ፍትሃዊ የታክስ አስተዳዳር ስርዓት ሰፍኖ አገራዊ ወጪ በአገራችን ገቢ ተሸፍኖ ማየት፡፡"

የባለስልጣኑ ተልዕኮ

5. “ታክስና ቀረጥን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር፣ ህግን ሊያስከብር የሚችል ሙያዊ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው ባለሙያ በመጠቀም፤ ዘመናዊ የታክስ እና ቀረጥ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት፣ ለሃገር እና ለከተማ አስተዳደር ልማት የሚውል ገቢ በብቃት በመሰብሰብ የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ማረጋገጥ”

የባለስልጣን መ/ቤቱ ዓላማ ስልጣን እና ተግባር

ዓላማ

6. በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የባለሥልጣኑ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዘመናዊ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
- ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣
- ኮንትሮባንድንና የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕግጋትን ማስከበር፣
- ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣
- የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ናቸው፡፡

የባለስልጣኑ መ/ቤት ስልጣንና ተግባር

7. ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መካከል ዋና ዋናዎቹ ፡-

- ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፡
- በመስኩ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስና የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡
- ግብር/ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ግብር/ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዘቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይተምናል፤ ተከፋይ የሚሆነውን የታክስ መጠን ይወስናል፤ ይሰበስባል፣

- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል የበለጠ አጽንኦት በመስጠትና ሌሎች ገቢዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ በጥናትና ምርምሩ ውጤት መሠረት ፖሊሲዎችንና ህጎችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
- ለገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤ ይከሳል ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቤያነ ሕግና መርማሪዎች ቡድን ያደራጃል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፤ ዘመናዊ የዕቃዎችና የሠነዶች ምርመራ አገልግሎት ላብራቶሪ ያደራጃል፤ በጥቅም ላይ ያውላል፣
- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የጉምሩክና የታክስ ወንጀሎችን የመመርመር፤ የመክሰስና ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር እንዲሁም ታክስ የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል ለክልል የፍትህ አካላትና ገቢ ሰብሳቢ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ለአፈፃፀሙ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣
- ለክልል ገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣
- የታክስና የጉምሩክ አስተዳዳርን በሚመለከት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣
- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣንና ለጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

8. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሚኒስትር ማዕረግ በአንድ በዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን በስሩ አምስት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና ተጠሪነታቸው ለዋና ዳይሬክተሩ የሆኑ አራት ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ለየዘርፉ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ተጠሪ የሆኑ 21 ዳይሬክተሮች አሉት፡፡ እንደዚሁም 30

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ 2 ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች፣ በባለስልጣን መ/ቤቱ በማኔጅመንት ውክልና የሚተዳደሩ 153 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይክሮ ግብር ከፋዮች ወረዳዎች ጽ/ቤት እና ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ የታክስ መሰብሰቢያ ማዕከላት 22 መቅረጫ ጣቢያዎች እና 50 መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በመያዝ ተደራጅቷል፡፡(አባሪ 2)

የሰው ኃይል

9. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋናው መ/ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሐምሌ 2005 ዓ.ም. 4,229 ወንድ 4,046 ሴት በድምሩ 8,275 ሠራተኞች የነበሩ ሲሆን፣ በመዋቅሩ መሰረት 7029 ክፍት የሥራ መደቦች ነበሩ፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

10. የባለስልጣን መ/ቤቱ ሥራውን የሚያንቀሳቅሰው ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኬጃ ለካፒታል በጀት ከመንግስት በሚመደብለት በጀት እና ከተለያዩ ለጋሽ አካላት ከሚገኘው እርዳታ ነው፡፡ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ገቢውን የሚሰበስበው ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ (ከወጪ እና ገቢ ንግድ ዕቃዎች)፣ ከሀገር ውስጥ ገቢ ግብር፣ ከብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የተጣራ ትርፍ እና ከኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ ነው፡፡በዚሁ መሰረት ከ2003-2005 በጀት አመታት የተመደበለት በጀት፣ በስራ ላይ ያዋለው ሂሳብና በነዚሁ በጀት ዓመታት የተያዘው የገቢ ዕቅድ እና የተሰበሰበው ገቢ ከታች ባለው ሰንጠረዠ የተገለጸ ሲሆን ከኮንትሮ ባንድ ዕቃ ሽያጭ የሚገኘውን ገቢ በተመለከተ በዕቅድ የማይያዝና አፈጻጸሙም የማይታይ በመሆኑ በሰንጠረዥ ውስጥ አልተካተተም፡፡

በጀት ዓመት	በጀት አጠቃቀም			በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበሰ ገቢ		
	የተፈቀደ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ	የገቢ ዕቅድ በሚሊዮን	የተሰበሰበ ገቢ በሚሊዮን	በመቶኛ
2003	595,614,423.97	564,163,943.98	94.71	54178.53	50816.45	93.79
2004	436,210,700.00	605,682,508.29	138.85	76367.08	70745.94	92.64
2005	541,522,700.00	730,369,871.71	134.87	101658.83	84414.41	83.04

የክዋኔ ኦዲቱ አላማ

11. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተዘረጋው የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት መረጃዎችን በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ ለመለዋወጥ የሚያስችል ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ ውጤታማ ሆኖ ካልተገኘ ውጤታማ እንዳይሆን ያደረጉትን ምክንያቶች ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማቃለል ወይንም ለማስወገድ

የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ እና ባለስልጣን መስያቤቱ ያለበትን ተጠያቂነት ለማጠናከር ነው ፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

12. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎች (EGAS) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡

13. ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002 - 2005 በጀት ዓመት ያለውን የባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃ አስተዳደር እና አያያዝ ስርዓት ሲሆን፣ ኦዲቱ የተከናወነዉ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ስር ተመዝግበው ከሚገኙ ግብር ከፋዮች በናሙና በተመረጡ በከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ በባህርዳር፣ በሀዋሳ፣ በምእራብ እና በምስራቅ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም ከአማራ ክልል የገቢዎች ጽ/ቤት እና ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ገቢዎች ባለስልጣን በናሙና መርጦ መረጃዎችን በመከለስ፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችም ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና አሠራሩን በአካል ተገኝቶ በመመልከት ነው፡፡

የኦዲቱ አካባቢ

14. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነውን የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት ጊዜና ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

15. በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነውን የታክስ መረጃ አስተዳደር ስርዓት ጊዜና ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ በሚለው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች(Audit issue) ተለይተዋል፡፡

እነርሱም፡-

1. የግብር መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና አስተዳደር ስርዓት በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ወጪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀትና ለመለዋወጥ በሚያስችል እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣
2. መረጃን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራርና የድጋፍና ክትትል ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑንና ሂደቱ ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

16. ከላይ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚያስችሉ 26 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የባለስልጣን መ/ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ የታክስ መረጃ አስተዳደር የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት እና የግብር ከፋዩን የመረጃ አያያዝና አሰባሰብን በተመለከተ የተዘጋጁ አዋጆችና ማስፈፀሚያ ደንቦች እንዲሁም አመታዊ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ናቸው፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር (በአባሪ 1) ተያይዟል፡፡

የታክስ መረጃ አስተዳደር የስራ ሂደት ስዕላዊ መግለጫ



ክፍል ሁለት

ግኝቶች

I. የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና የአስተዳደር ስርዓት የተጣጣመ ወጥ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥን በተመለከተ፡፡

ዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀትና አስተዳደር መኖሩን በተመለከተ፤-

17. የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የገቢ አሰባሰብና የታክስ አወሳሰን ሂደት በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የተደገፈ የታክስ መረጃ አሰባሰብና፤ አደረጃጀት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
18. ባለስልጣን መ/ቤቱ በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ግብር ከፋዮች መረጃ በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ በዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀትና አስተዳደር ለመያዝ የሚያስችል የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በእያንዳንዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተያዘ መረጃን የሚመዘግብና የሚቆጣጠር፤ የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥርና የጣት አሻራ መመዝገቢያ እና የጉምሩክ ቀረጥ አከፋፈልን የሚያግዝ አሲኩዳ የተባሉ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችን የዘረጋ ቢሆንም በዘረጋው የመረጃ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ በአግባቡ የግብር ከፋዩን መረጃ አሰባስቦ የመያዝ የማደራጀት እና የማስተዳደር ተግባሩን በቂ ትኩረት ሰጥቶት ተግባራዊ አድርጎት አልተገኘም፡፡
19. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ ባህርዳር፣ የምዕራብ አዲስ አበባ፣ በምስራቅ አዲስ አበባ፣ በሀዋሳ ቅ/ፅ/ቤቶች እንደተመለከትነው የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) ሪከርድ ማኔጅመንት ሞጁል በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ አለማዋሉን፣ በማህደር ተከማችተው ያሉ የግብር ከፋይ መረጃዎችን በማጥራት ወደ ተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) ሙሉ በሙሉ ተመዝግበው ያልገቡ እና በSIGTAS ላይ ያለው የግብር ከፋይ መረጃ በመዝገብ ቤት በማህደር ከተያዘው ጋር የማይናበብ መሆኑን፣ እንዲሁም በመዝገብ ቤት የተያዘው የግብር ከፋይ ማህደር በቂ ቦታና እና የፋይል ማስቀመጫ (ላተራል) ያልተዘጋጀለት በመሆኑ ለአደጋ የተጋለጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል ፡፡
20. ስለጉዳዩ በናሙና የታዩት የሐዋሳ፣ የባህርዳር፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የምስራቅ አዲስ አበባ እና የምዕራብ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የግብር ከፋዮች መረጃ በሙሉ ተጠቃሎ ወደ SIGTAS እንዲገባ የተደረገ ቢሆንም ወደ የገባው SIGTAS መረጃ በትክክል ያልገባ በመሆኑ በግብር ከፋዩ ማህደር (hardcopy)

ያለው እና በSIGTAS ላይ ያለው የግብር ከፋይ መረጃ በአብዛኛው የማይናበብበት ሁኔታ በመኖሩ የጠራ እና ወቅታዊ መረጃ ማግኘት የማይቻል መሆኑን፤ በSIGTAS የተያዘውን መረጃ ለግብር አወሳሰንም ሆነ ለታክስ ኦዲት እንዲሁም ለቅሬታ ውሳኔዎች መሰረት አድርጎ ለመጠቀም እንደተቸገሩ ገልጸዋል፡፡

21. ይህንንም በተመለከተ የቅ/ፅ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የታክስ አስተዳደር የተጀመረው በተጨማሪ እሴት ታክስ መሆኑን፤ ሁሉንም የታክስ ዓይነቶች SIGTAS በመጠቀም ማስተዳደር የተጀመረው በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ተሞክሮ ውጤታማነቱ ከታየ በኋላ በየደረጃው ወደ መካከለኛና አነስተኛ እንዲሁም ማይክሮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እየሰፋ እንደሚገኝ፣ ሂደቱ የተጠናቀቀ አለመሆኑ፣ "SIGTAS"ን ተጠቅሞ ታክስ ለማስተዳደር የራሱ ሥልጠናዎች ስለሚያስፈልጉት ተከታታይና ቀጣይነት ያለው ሥልጠና እየተሰጠ ሥርዓቱን የመጠቀም አቅም በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

22. የባለሥልጣኑ የኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ደግሞ ችግሮቹ በሥራ ላይ ያሉትን ሞጁሎችም በአግባቡ ካለመጠቀም እንዲሁም ከመረጃዎች ማጥራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በመሆናቸው የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

23. የተዘረጋው የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ የግብር አወሳሰኑን ቀልጣፋ እና ፍትሃዊ እንዳይሆን በማድረግ መሰብሰብ ያለበት ገቢ እንዳይሰበሰብ እንቅፋት ይሆናል፡፡

የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር አሰጣጥን በተመለከተ

24. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ግብር ከፋዮች መረጃ በየደረጃው መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት እያንዳንዱ ግብር ከፋይ በጣት አሻራ ላይ የተመሠረተ የግብር ከፋይ የመለያ ቁጥር (TIN) ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዳይኖረው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

25. ባለስልጣን መ/ቤቱ በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ ስርዓት አፈፃፀም መመሪያ 11/2001 አውጥቷል፡፡ በመመሪያውም ላይ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ መለያ ቁጥር ሊሰጠው እንደማይችል ያስቀምጠ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡት ቅ/ፅ/ቤቶች 26 የሚሆኑ ግብር ከፋይዎች በሁለት መለያ ቁጥር (TIN) ተመዘግበው ተገኝተዋል፡፡

26. ስለሁኔታው የቅ/ፅ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የግብር ከፋዮች መለያ (TIN) ትግበራ ፕሮጀክት በመዘግየቱና ለተጨማሪ እሴት ተመዝጋቢ ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፊኬት መስጠት ግዴታ በመሆኑ ሰርተፊኬቱን ለመስጠትም የግብር ከፋዩን መለያ ቁጥር መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ "Fictitious TIN" እየተሰጠ ሰርተፊኬቱ እንዲወጣ የተደረገ በመሆኑ ትክክለኛው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠት ሲጀምር አስቀድመው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ሲባል ከተሰጣቸው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ሌላ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በመሰጠቱ መሆኑን፣ በተጨማሪም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) የሚፈጠረው ለሲስተሙ በሚሰጠው በእንግሊዘኛ ፊደል በተፃፈ የግብር ከፋይ ስም በመሆኑ በአንድ የፊደል ለውጥ ምክንያት ለአንድ ሰው ሌላ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) የሚወጣበት ሁኔታ መኖሩን፣ በተለያዩ አድራሻዎች የንግድ ሥራ የሚያካሂዱ በአንድ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) የመጠቀም ግዴታ ሲኖርባቸው ካለመገንዘብም ይሁን ሆን ብለው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ማመልከቻ ሲያቀርቡ የስም ፊደል አፃፃፍን መጀመሪያ ከሰጡት ለየት አድርገው ሞልተው በማቅረብ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለአንድ ግብር ከፋይ የተሰጠበት ሁኔታ በመፈጠሩ መሆኑን፣ ይህንን ለማስቀረት TIN በጣት አሻራ እንዲደገፍ ለማድረግ ፕሮጀክት ተቀርፆ ከ2003 በጀት ዓመት የመጨረሻው ሩብ ዓመት ጀምሮ የማጥራት ሥራው እየተካሄደ ሲሆን፤ እስካሁን ቀርበው የጣት አሻራ በመስጠት የቀድሞው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) እንዲቀር ያላደረጉ በመኖሩ በ system በሚታየውና በተጨባጭ በግብር ማዕከላቱ ያሉት ግብር ከፋዮች ቁጥር ልዩነት የሚያሳይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

27. ይህንንም በተመለከተ የባለሥልጣኑ የኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ግብር ከፋዮች ለምዝገባ በሚመጡበት ወቅት አስቀድመው መመዝገባቸውና አለመመዝገባቸውን ካለማጣራት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የመረጃ ማጥራት ተካሂዶ የሚስተካከል መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

28. ለአንድ ገብር ከፋይ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መሰጠቱ ግብር ከፋዩ መክፈል የሚጠበቅበትን ግብር እንዲሰውር በር በመክፈት መሰብሰብ በሚገባው የመንግስት ገቢ ላይ አሉታዊ ተፅኖ ያሣድራል፡፡

ግብር ከፋዮች የመክፈያ ጣቢያ ሲቀይሩ መረጃቸው የሚተላለፍ መሆኑን በተመለከተ

29. ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት/ ጣቢያ ሲቀይሩ በሰነድ ያለው መረጃ ሙሉ ለሙሉ መዘዋወሩ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ እና በSIGTAS ያለው የመክፈያ ጣቢያ መለያ ቁጥርም ወደ አዲሱ መቀየሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

30. በኦዲቱ ወቅት 62 ግብር ከፋዮች በተቋሙ ስር ከሚገኙት 10 የታክስ ማዕከሎች ውጭ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 25 ግብር ከፋዮች “አዲስ አበባ ቫት” በሚባል የተመዘገቡ ሲሆን፣ 37 ግብር ከፋዮች “አዲስ አበባ ገቢዎች ባለስልጣን” በተባለ በተዘጋ ታክስ ማእከል የተመዘገቡ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅ/ጽቤት (ታክስ ማዕከሎች) በሚቀይሩበት ወቅት ፋይላቸው ከነሙሉ መረጃቸው መዘዋወር አለመዘዋወሩን ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋ እና ለዝውውር ሂደቱ የተቀናጀ የመንግስት የታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)ን አለመጠቀማቸው በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡

31. ሰለሁኔታው የድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የአገራችን የታክስ አስተዳደር በተቀናጀ የመንግሥት ታክስ አስተዳደር ሥርዓት መታገዝ ሲጀምር የተፈጠረው የታክስ ማዕከል አዲስ አበባ ቫት በሚል በመሆኑ፣ በዚያን ወቅት በመረጃና በግዳጅ የምዝገባ ሥርዓት እንዲመዘገቡ ተደርገው አካውንት የተከፈተላቸው ሲሆን፣ ወደ ተለያዩ የታክስ ማዕከላት ክፍፍል ሲደረግ በተመዘገበው አድራሻ ያልነበሩ በመሆናቸው ይኸው ተፈትሾ ባለመዘጋቱ መሆኑን፣ የSIGTAS ፕሮጀክትን ተግባራዊ ለማድረግ ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ለመክፈል ወደ ሚመርጡት አዲስ ወደተከፈቱት የታክስ ማዕከላት እንዲስተናገዱ ሲደረግ በተደረገው የመረጃ ልውውጥ ወቅት ያልተካተቱ ግብር ከፋዮች ሊሆኑ ስለሚችሉ እነዚህ ግብር ከፋዮች ባስመዘገቡበት አድራሻ በተጨባጭ የሚሠሩበት ሥራ ተፈትሾ በማረጋገጥ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት ዕቅድና የድርጊት-መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ የሚተገበርበት አቅጣጫ እየታየ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

32. ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ጣቢያ ሲቀየሩ መረጃቸው ሙሉ በሙሉ መዘዋወሩ የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በግብር ከፋዩ ላይ እንግልት፣ ለአላስፈላጊ የጊዜና የወጪ ብክነት የሚዳርግ ሲሆን፣ በተጨማሪም የተዛባ የግብር ውሳኔዎችን እንዲተላለፉ እና መንግስት መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ በአግባቡ እንይሰበሰብ በር ይከፍታል፡፡

በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (በSIGTAS) እና በቅ/ፅ/ቤቶች የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ ተመሳሳይና የሚናበብ መሆኑን በተመለከተ

33. በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) በማዕከል ተመዝግቦ የተያዘው የግብር ከፋዮች መረጃ በቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች (የታክስ ማእከል) ተመዝግቦ ከተያዘው የግብር ከፋይ መረጃ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል፡፡

34. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት አምስት የታክስ ማዕከላት በግብር ከፋይነት ተመዝግበው የተያዙት 21595 ግብር ከፋዮች ሲሆኑ፣ በማዕከል በተቀናጀ የመንግስት የታክስ

አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS) በአምስቱ ቅርንጫፎች ያሉ ተብሎ ተመዘገቦ የተያዘው 29792 ግብር ከፋዮች መሆናቸው፣ ይህም በማእከል በSIGTAS ተመዝግቦ የተያዘው በ8197 በብልጫ የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል ፡፡

35. ከላይ ከተጠቀሱት ግብር ከፋዮች ውስጥ በአምስቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በስራ ላይ ያሉ (Active) ተብለው የተያዙ 20047 ግብር ከፋዮች ሲሆኑ በSIGTAS ላይ በሥራ ላይ ያሉ ግብራቸውን የሚያሳውቁ (active) ተብለው የተያዙት 28,287 ግብር ከፋዮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም በ(active) በግብር ከፋይነት በSIGTAS ላይ የተመዘገቡት ግብር ከፋዮች በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተመዝግበው ከያተዙት በ8240 ግብር ከፋይ በብልጫ በልዩነት ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በባህርዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በግብር ከፋይነት የተመዘገቡ 37 ግብር ከፋዮች በSIGTAS ላይ ምዝገባቸው በሌላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት (የታክስ ማዕከል) ላይ ተመዝግበው የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስም	ጠቅላላ የግብር ከፋይ ብዛት		ልዩነት	የሚታወቁ ሥራ ላይ ያሉ (ACTIVE) ግብር ከፋዮች		ልዩነት
	ዋናው ዳታ ቤዝ በታክስ ማዕከል አለኝ የሚለው	በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ		ዋናው ዳታ ቤዝ በታክስ ማዕከል አለኝ የሚለው	በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ	
አ.አ ምስራቅ	14026	11212	2814	13423	11157	2266
አ.አ ምዕራብ	10796	6783	4013	10128	5998	4130
ከፍተኛ ግብር ከፋዮች	1354	886	468	1341	873	468
ባህር ዳር	2338	1561	777	2132	1020	1112
ሐዋሳ	1278	1153	125	1263	999	264
ድምር	29792	21595	8197	28287	20047	8240

36. ስለጉዳዩ የባለሥልጣኑ የኦፐሬሽን ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በማህደር ያለው (Hard copy) እና በ SIGTAS የተያዙ መረጃዎች ያለመናበብ ሁኔታ የተፈጠረው ግብር ከፋዮች ለምዝገባ በሚመጡበት ወቅት አስቀድመው መመዝገባቸውና አለመመዝገባቸውን ካለማጣራት ጋር የሚያያዝ በመሆኑ የመረጃ ማጥራት ተካሂዶ የሚስተካከል መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

37. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያሉትን ግብር ከፋዮች ብዛትና የት ግብር እንደሚከፍሉ በትክክል አለማወቁ ትክክለኛውን የግብር ከፋይዎች ቁጥር እንዳያውቅ ከማድረጉም በላይ በመረጃ ላይ የተደገፈ የገቢ አሰባሰብ ዕቅድ እንዳያቅዱ እና መሰብሰብ የሚገባው የግብር ገቢ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ ያደርጋል፡፡

የግብር ከፋዮች የግዥ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ተጠናቅረው በመረጃ ቋት /Data Base/ በማእከል መያዛቸውን በተመለከተ

38. የተሟላ መረጃን መሰረት ያደረገ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ከሁሉም ግብር ከፋዮች እና ከሶስተኛ ወገን መረጃ ሰጪ አካላት የግዢ እና የሽያጭ ግብይት መረጃዎች ተሰብስበው እና ተደራጅተው በመረጃ ማእከል /ቋት/ ሊያዙ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የግብር ከፋዮች የቅሬታ መረጃዎች እና የተሰጡ ውሳኔዎች በተደራጀ ሁኔታ ተጠናቅሮ ሊያዝ ይገባል፡፡

39. በኦዲቱ ወቅት የሁሉም ግብር ከፋዮች የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች እና የ3ኛ ወገን መረጃዎች በተሟላ መልኩ የማይሰበሰቡና የተሰበሰቡትም መረጃዎች በተሟላ ሁኔታ በማዕከል ደረጃ ወደአለው የመረጃ ቋት ተጠቃሎ አለመግባቱን፣ በተለይም የ2003 እና የ2004 በጀት ዓመታት የግዢ እና የሽያጭ የግብይት መረጃዎች ግን ሙሉ በሙሉ ወደ መረጃ ቋት አለመግባታቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የግብር ከፋዮች መረጃ ለውሳኔም ሆነ ለሌሎች ተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ እንደ የሥራ መስኩ እና ዓይነት እየተለዩ (ለምሳሌ በግብርና ዘርፍ፤ በኮንስትራክሽን ዘርፍ፤ በኢንዱስትሪ ዘርፎች ወዘተ--) ተደራጅተው እንዳልተያዙ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

40. ውዝፍ ዕዳ ያለባቸውን ግብር ከፋዮች፣ ግብር ከፋዮች የሚያቀረቡትን የቅሬታና አቤቱታ የሚመለከቱ መረጃዎች፣ የተሰጡ ውሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃችን የሚገልጹ መረጃዎች በተደራጀ ሁኔታ ተጠናቅረው አለመያዛቸው ታውቋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መረጃው በሚመዘገብበት ወቅት ግብር ከፋይ ማቅረብ የሚገባቸው ዋና ዋና መረጃዎች እንደ የባንክ አካውንት፣ የተሰማሩበት የስራ ዘርፍ፣ የግብር እፎይታ ጊዜ ተጠቃሚ ከሆኑ ደግሞ ዕፎይታው የሚያልቅበት ጊዜ እንዲሁም ወቅታዊ አድራሻዎች በተሟላ ሁኔታ በSIGTAS አለመመዝገቡን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የግብር እፎይታ ጊዜ (Tax holiday) ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የዕፎይታ ጊዜያቸው መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚያበቃና ያሉበትን ደረጃ የሚገልጽ መረጃና ሌሎች መረጃዎች በተሟላ መልኩ ተደራጅተው አለመያዛቸውን ባለሥልጣኑ ያቋቋመው አገር ውስጥ ታክስ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ቡድኑ ሪፖርት ላይም ተገልጿል፡፡

41. ስለሁኔታው የታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ እስከ መስከረም 2005 ባጋጠማቸው የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት የግብይት መረጃዎች ወደ መረጃ ቋት ተጠቃለው አለመግባታቸውን፤ በአሁኑ ወቅት ግን የተሰበሰቡ የግዥ መረጃዎች በመረጃ ቋት እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑንና በቅ/ጽ/ቤቶች የተሰበሰቡ የተወሰኑ መረጃዎች በተሰጣቸው ቅፅ መሰረት በአግባቡ ባለመሙላታቸው ወደ መረጃ ቋት አለመግባታቸውን፤ ከአምራቾችና ከአስመጪዎች የተሰበሰበው መረጃ እንደ የሥራ መስኩ

እና ዓይነት በመረጃ ቴክኖሎጂ ግብአት ባለሟላትና ባለመጠናቀቅ ምክንያት መረጃውን ሰብስቦ በSIGTAS ማደራጀት እንዳልተቻለ እና የሽያጭ መረጃዎች ወደ መረጃ ቋት በተሟላ መልኩ እየገቡ ያለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

42. በተጨማሪም ውዝፍ ዕዳ ያለባቸውን ግብር ከፋዮች የሚመለከቱ መረጃዎች እና የግብር ከፋዮችን የቅሬታ መረጃዎች በአግባቡ መያዙን በተመለከተ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በየዓመቱ የቀረቡ፣ የተስተናገዱና ለቀጣይ አመት የዞሩ ተብለው የሚያዙና በሪፖርትም የሚገለጹ ሲሆን በSIGTAS የመመዝገብ ሁኔታ አለመጀመሩን ገልፅዋል፡፡ ሆኖም የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው የሚያስተላልፈውን መረጃ እንደግብዓት መጠቀም ስለሚቻል የቴክኖሎጂ ግባአት ችግር ነው ተብሎ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

43. ይህ በመሆኑ ከግብር ከፋዮ የሚፈለጉ ውዝፍ ዕዳዎችን መጠን እንዳይጣወቅ፣ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ እንዲሁም በመ/ቤቱ የታክስ ኦዲት ተግባር ላይ ተፅኖ በማሣደር የተዛባ ውሣኔ እንዲሰጥና መሰብሰብ የሚገባው ገቢ እንዳይሰበሰብ ያደርጋል፡፡

የግብር ከፋዮዎች ሀብትና ንብረት መረጃ ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

44. ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ መረጃ እንዲኖር የሁሉም ግብር ከፋይ ሀብትና ንብረት ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

45. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአጠናው የመሰረታዊ የአሰራር ስርዓት ለውጥ ጥናት የሁሉም ግብር ከፋይ ሀብት እና ንብረት ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት እንደዘረጋ ቢገለፅም በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ የሁሉንም ግብር ከፋዮች ሀብትና ንብረት መዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

46. ስለሁኔታው የታክስ መረጃ አያያዝ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የሀብትና ንብረት መረጃ መመዝገቢያ ሥርዓት ተዘርግቶ እየተተገበረ እንደሚገኝ እስከ አሁንም ከግል ባንኮች እና ኢንሹራንሶች የድርጅቶችን የአክሲዮን ድርሻ፣ ከመሬት አስተዳድር በድርጅቶች ስም የተመዘገበ መሬትና ቤት፣ ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን በድርጅቶች ስም የተመዘገቡ መኪናዎችና ከከተማና ልማት ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በድርጅቶች ስም የተመዘገቡ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችና መኪናዎች መረጃ መሰብሰቡን፣ በዚህ አመትም ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እቅድ መያዙን ሆኖም እነዚህ መረጃዎች በሲስተም ያልተደራጁ በመሆኑ ሶፍት ዌር በማስቀረጽ የመረጃው ተጠቃሚዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በቀጥታ (online) መረጃዎችን ማግኘት እንዲችሉ ለማድረግ እቅድ መያዙን ገልጸዋል ፡፡

47. ዳይሬክተሩ ይህን ቢሉም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው የአዋሳ፣ የባህርዳር፣ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የምዕራብና የምስራቅ ቅ/ፅ/ቤቶች ሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በተቋም ደረጃ የግብር ከፋይ ሀብትና ንብረት ለማወቅ የሚረዳ የመመዝገቢያ ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

48. በባለስልጣን መ/ቤቱ ሥር የሚገኙ የግብር ከፋዮች መረጃ በመረጃ ማዕከል በአግባቡ ባለመያዙ ምክንያት የተሟላ መረጃን መሠረት ያደረገ የግብር አወሳሰን አሰባሰብ ስርዓት እንዳይኖር የሚያደርግ ሲሆን፣ የግብር ከፋዮችን ሀብትና ንብረት ለመመዝገብ የተዘረጋው ሥርዓት በማዕከል በዋናው መ/ቤት እየተሰራ መሆኑን ቢገለፅም ገና በጅምር ላይ ያለ መሆኑ፣ እንደተቋም በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ባለመሆኑ በውዝፍ የግብር ዕዳ አሰባሰብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረጉ መሆኑን በተመለከተ

49. በመረጃ ዳታ ቤዝ /ቋት/ ተደራጅቶ የተያዘው መረጃ እና በመዝገብ ቤት በማህደር (Hard Copy) የተያዘው የግብር ከፋይ መረጃ በየጊዜው እየተገመገመ ወቅታዊ ሊሆን ይገባል፡፡

50. በኦዲቱ ወቅት በመዝገብ ቤት በማህደር ተይዘው የሚገኙ መረጃዎችን የማጥራት ተግባር እንዳልተከናወነ እና በSIGTAS ተመዝግበው የተያዙ የግብር ከፋይ መረጃዎች በየጊዜው እየተገመገመ ወቅታዊ የማይደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 እና በተሸሻለው አዋጅ ቁጥር 608/2001 መሰረት ግብር ከፋዩ የሚያደረጋቸውን ማንኛውም ለውጦች በግብር ከፋይነት በተመዘገበቡበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እየቀረበ ማሳወቅ እንደሚገባው እና በየጊዜው የማያሳውቁ ግብር ከፋዮች ተጠያቂ ሊደረጉ እንደሚገባ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ተግባራዊ ተደርጎ አልተገኘም፡፡

51. ስለ ሁኔታው የቅ/ፅ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክተር ለቀረበላቸው መጠይቅ በመረጃ ቋት የተያዘው መረጃ ወቅታዊ መደረግን አስመልክቶ የሰጡት መልስ የለም፡፡

52. በመረጃ ቋት የተያዘው መረጃ እና በመዝገብ ቤት በማህደር የተያዘው መረጃ ወቅታዊ ያለመደረግ ግብር ከፋዩን በቀላሉ ለማግኘት ካለማስቻሉም በላይ የተዛባ የግብር ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዲፈጠር እና መሰብሰብ የሚገባው ግብር እንዳይሰበሰብ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

የታክስ መረጃ አሰባሰብና አስተዳደር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መዘጋጀቱን በተመለከተ

53. ባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃ ለማሰባሰብ ፣ለማደረጀት እና ለማሰተዳደር በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ፖሊሲና እስትራቴጂ መቅረጽ እና የተቀረፀውን ፖሊሲና

ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎች (ማንዋሎች) አዘጋጅቶ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆኑ ሊያደረግ ይገባል፡፡

54. በኦዲቱ ወቅት ባለስልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃዎችን በአይነታቸው እየለየ ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀት እና ተንተኖ በማሰራጨት ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም አገር አቀፍ የግብር መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ወጥ እና ተመጋጋቢነት ያለው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

55. ይህንንም በተመለከተ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመረጃ ማኔጅመንት (data management) ፖሊሲ ረቂቁ ተዘጋጅቶ በበላይ አመራር እንዲታይና ውሳኔ አግኝቶ ሥራ ላይ እንዲውል መቅረቡን፣ ፖሊሲውን ለማዳበርም የውጭ አገር ልምድ መቅሰም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሁኔታዎች እየተመቻቹ በመሆኑ ፖሊሲው ጸድቆ ሥራ ላይ አለመዋሉን፣ የመረጃ ደህንነት ፖሊሲ ግን በባለሥልጣኑ ተዘጋጅቶና ጸድቆ ሥራ ላይ መዋሉን፣ ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ የመረጃ አሰባሰብ፣ ጥንቅርና ስርጭት፣ አጠቃቀምና ግብረ-መልስ ስርዓት ለመዘርጋትና ተግባራዊ ለማድረግ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት ተጠናቆ በማፀደቅ አደረጃጀት ተፈቅዶ የሰው ኃይል ተመድቦ ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ አለማድረጉን ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ለበላይ አመራር ለውሳኔ ቀርቧል የተባለው የመረጃ አስተዳደር ረቂቅ ፖሊሲ በኦዲት ወቅት ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

56. የታክስ መረጃን ለመሰብሰብ ፣ለማደራጀት እና ለማስተዳደር እንዲሁም በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ፖሊሲ እና ስትራቴጂ አለመቀረፁ እና የተቀረፀውን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎች /ማንዋሎች/ ተዘጋጅተው በፌዴራልም ሆነ በክልል ተግባራዊ እንዲሆኑ ያለመደረጉ ወጥ የሆነ የግብር አሰባሰብ እና የመረጃ ሥርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

በፌዴራል፣ በክልል መንግስት እና በከተማ መስተዳደሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ መኖሩን በተመለከተ

57. በፌደራል፣በክልል መንግስታት እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል ወጥነት ያለው የታክስ መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር እንዲኖር የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ሊኖር ይገባል፡፡

58. በኦዲቱ ወቅት በክልሎች እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ለመፈራረም በእቅድ የተያዘ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

59. ስለሁኔታው የታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የስምምነት ሰነድ ያልተፈረመበት ምክንያት በባለስልጣኑ የታክስ መረጃ አስተዳደር የስምምነት ሰነድ አዘጋቶ ለአስተያየት ለሚመለከታቸው ክልሎች ተልኮ ምላሽ ባለማግኘቱ ምክንያት ሰነዱን መፈራረም አለመቻሉን፣ ይህ አለመሆኑ ደግሞ የመረጃ ክፍል የሌላቸው ክልሎች የመረጃ አስተዳድር እንዲኖራቸው በማድረግ ለመደገፍ፣ ያላቸው ደግሞ በተጠናከረ ሁኔታ በአካባቢያቸው ካሉ ግብር ከፋዮች መረጃ ሰብስበው እንዲያደራጁ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ እና የልምድ ልውውጥ ለማድረግ አለማስቻሉን ገልጸዋል፡፡ ስለ አደረጃጀትና መዋቅር እንዲያስቡበት የሚያደርግ የታክስ መረጃ አስተዳደር ጠቀሜታና የትኩረት አቅጣጫ የሚል ጽሁፍ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በታህሳስ 12 እና 13 2005 ዓ/ም በጅጅጋ ከተማ ባዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ ለማቅረብ ጥረት መደረጉን፣ በዚሁ የምክክር መድረክ የተፈረመውን አገር አቀፍ ስምምነት መነሻ በማድረግ አስተያየት እንዲሰጡበት ለየክልሎቹ መላኩን፣ ይህ ስርዓት ባለመዘርጋቱ ምክንያት ከክልሎች እና ከከተማ አስተዳደሮች የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘት አለመቻላቸውን ባጠቃላይ ጠንካራና አስተማማኝ የግብር ከፋይ የመረጃ ስርአት አለ የሚባለው በሁሉም ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች መረጃዎች እየተሰበሰቡ በአግባቡ ሲደራጁና እና የተጠናከረ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ሲኖር መሆኑን፣ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ግን የተማላ መረጃ ተይዟል ለማለት እንደማያስደፍር ገልፀዋል ፡፡

60. የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር እንዲኖር የሚያግዝ የታክስ መረጃ አስተዳደር የመግባቢያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያለመደረጉ ሀገራዊ የሆነ የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር እንዳይኖር እና የእርስ በርስ የልምድ ልውውጥን በማድረግ ሀገሪቱ ልታገኝ የምትችለውን ገቢ አሟጦ የመሰብሰብ ሂደቱን ይቀንሰዋል ፡፡

የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆኑ የሚገባቸው ግብር ከፋዮችን በተመለከተ

61. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች በሙሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መርሃ-ግብር መሰረት መሳሪያውን መጠቀም አለባቸው፡፡

62. በደንቡመሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን መጠቀም ያለባቸው ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዮት በከፍተኛ ግብር ከፋዮች በባህርዳር፣በሀዋሳ፣ በምዕራብና በምስራቅ አ/አ ቅ/ጽ/ቤቶች በSIGTAS ተመዝግበው ከተያዙት 29792 ግብር ከፋዮች ውስጥ 12090 ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ተጠቃሚ ሲሆኑ 17702 (59.41%) ግብር ከፋዮች ተጠቃሚ ያለመሆናቸው ታውቋል፡፡

63. ስለሁኔታው የታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በስጡት ምላሽ በመርሃ-ግብሩ መሰረት በመጨረሻ ዙር መሳሪያ መጠቀም የሚገባቸው ተብለው በማስታወቂያ የወጣው የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች መሆናቸውን፣ በዚህ መርሃ-ግብር መሰረት በተጠቀሰው ደረጃ የሚገኙ ግብር ከፋዮች የመጠቀም ግዴታ ከሌለባቸው ንግድ ስራዎች በሰተቀር በሙሉ እንዲጠቀሙ መደረግ ይገባቸው እንደነበረ ሆኖም በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የማስፈጸም አቅም ውስንነት በመኖሩ ተፈጻሚ ሊደረግ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

64. በደንቡ መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች በሙሉ ተጠቃሚ አለመሆናቸው ለግብር አወሳሰን በሚረዳ የግብይት መረጃ አሰባሰብና በገቢ አሰባሰብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌርን በተመለከተ

65. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌር በባለሥልጣን መ/ቤቱ ዕውቅና የተሰጠው ሊሆን ይገባል፡፡ በባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ያላገኘ ሶፍት ዌር የሚጠቀሙ ግብር ከፋዮች ካሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመከታተልና በመቆጣጠር ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

66. ባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ባልሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሶፍትዌር መጠቀም በህግ እንደሚያስጠይቅ በተሻሻለው የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 47 ቁጥር 1 ላይ የተገለፀ ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩ በከፍተኛ ግብር ከፋይነት የተመዘገቡ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ 14 ሆቴሎች ባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ባልሰጠው ሶፍትዌር እየተጠቀሙ መሆኑን እና ባለስልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መረጃቸውን በአግባቡ ማስገባታቸውንና መረጃው ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የመረጃ ቋት ጋር የተገናኘ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር የማያደርግ እና በህጉ መሠረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

67. ከዚህም በተጨማሪ በሂልተን እና በሸራተን አዲስ ሆቴሎች ከአገልግሎት ውጭ የተደረጉ 22 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች በመመሪያው መሰረት በአስመጪዎቹ ዘንድ መቀመጥ ሲገባው በሆቴሎቹ መጋዘኖች ውስጥ ለረዥም ጊዜ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

68. ይህን አስመልክቶ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ዕውቅና ባልተሰጠው ሶፍትዌር እንደሚጠቀሙ የሚታወቁት ድርጅቶች በዋነኛነት ትላልቅ ሆቴሎች ሲሆኑ በአገር ውስጥ ዕውቅና የተሰጣቸውን ሶፍትዌር መጠቀም እንደማይችሉ፣ በአለም ላይ በስራ ላይ የዋሉ ለኢንዱስትሪው ተመራጭ የሆኑ ሶፍትዌሮች ስላሉ እነዚህ እንዲፈተሹላቸውና በተለየ ሁኔታ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ ቢያቀርቡም በተለይም ክላይንት ሰርቨር ለሚጠቀሙ ተስማሚ የሆነ ሶፍት ዌር በባለሥልጣን መ/ቤቱ በነበረው የልምድና የአቅም ውስንነት ሳቢያ ሊዘጋጅ ወይም ፈትሾ እውቅና ሊሰጥላቸው ባለመቻሉ በወቅቱ በነበረው አማራጭ ኢንዱስትሪውን ከመጉዳትና ከመዝጋት ሳይፈቀድም ሳይከለከልም በዝምታ ስለታለፈ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ክላይንት ሰርቨር ለሚጠቀሙ የንግድ ሥራዎች የሶፍት ዌር ማሻሻያ በማድረግ ለፍተሻ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂና ምህንድስና ክፍል ተላላፎ በቦርዱ ዕውቅና ሲያገኝ ሥራ ላይ ለማዋል ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣ የሽያጭ መረጃ ክትትልን በተመለከተ በማሽኑ የሚወጣ ሪፖርትና በሶፍትዌሩ ውስጣዊ አሰራር ለሚፈጠር ያለመጣጣም ችግር (Interface Problem) የሚያጋጥማቸው ሶፍትዌሮች ችግራቸውን ለመፍታት ከሶፍትዌር አምራች ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ እንዲያገኝ ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

69. በመሳሪያዎች በብልሽት፣ በዓመታዊ ምርመራ፣ በአድራሻ ለውጥ፣ በስም ለውጥ፣ በመዝጋት ወይም በመዝጋት ሂደት ወዘተ… ላይ ጥያቄ ሲቀርብ ወደ አገልግሎት ማዕከል እንዲመለስ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት መኖሩን፣ ሆኖም መረጃ የሚልኩና የማይልኩትን በአስተማማኝ መልኩ እንደታሰበው የሚያረጋግጡበት ሁኔታ ባለመመቻቸቱ ሥራ ላይ በሌሉት ወይም መረጃ በማያስተላልፉት ላይ ክትትል በማድረግ ምክንያቱን ለማወቅ የሚቻልበትና ፊስካል ማስታወሻው በአገልግሎት ማዕከል እንዲቀመጥ የሚደረግበት ሁኔታ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

70. ለየሥራ ዘርፉ ተስማሚ የሆኑ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ሶፍት ዌር ለሁሉም የሥራ ዘርፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ህጋዊ በሆነ ሶፍት ዌር በሚጠቀሙ እና በማይጠቀሙ ድርጅቶች መካከል ፍታዊ የሆነ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ከማድረጉም በተጨማሪ ህጉ ተግባራዊ እንዳይደረግ እና ከድርጅቶቹ መሰብሰብ ያለባቸውን ቀጥተኛም

ሆነ ቀጥተኛ ያልሆኑ የታክስ ገቢዎች ሙሉ በሙሉ በባለሥልጣን መ/ቤቱ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

የሽያጭ መሳሪያዎች ጥገናን በተመለከተ

71. አቅራቢዎች የጥራት ደረጃውን የጠበቀ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ማቅረባቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መስፈርት ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ሲበላሹ በተበላሹ በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊደረግ፣ አገልግሎት ላይ ያሉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችም በየአመቱ መደበኛ ምርመራ ሊደረግላቸው እና መሳሪያዎቹን ለማቅረብ ግዴታ የገቡት አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ማቅረባቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊደረግና ግዴታቸውን በአግባቡ ባልተወጡ አቅራቢዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

72. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችም ሆነ አቅራቢዎቹ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 133/1999 መሰረት መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ሆኖም ግብር ከፋዩ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎች ገዝቶ ከሚጠቀምባቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በአማካይ በዓመት 15670 የሚሆኑት በብልሽት ምክንይት ለጥገና የሚገቡ ሲሆን 7146 (46%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሲወጡ የቀሩት 8320 (54%) በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው እንደማይወጡ፣ አገልግሎት ላይ ከዋሉ ከአንድ አመት በላይ የሆናቸው 72964 የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች አመታዊ ምርምራ በተሟላ መልኩ እንደማይደረግላቸው እና ባለሥልጣን መ/ቤቱም በህጉ እና በገቡት ግዴታ መሰረት ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎችን በመከታተልና በመቆጣጠር እርምጃ የማይወስድ መሆኑ ታውቋል፡፡ በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው የወጡ እና ያላወጡ የመሣሪያዎችያ አቅራቢዎች ዝርዝር በአባሪ (3) ተያይዟል፡፡



73. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በክልላቸው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪዎቹን ለመጠቀም በደንበኞቻቸው በኩል ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖርም የአቅርቦት ችግር መኖሩን፣ ብልሽት ሲያጋጥም በ48 ሰዓት ተጠግነው ስለማይመለሱ ግብር ከፋዮች እየተማረሩ መሆኑን እና መሳሪያዎቹ በብዛት እየተበላሹ በመሆናቸው ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ የሚደረገው ፍተሻ በአግባቡ ሊታይ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

74. ይህንንም በተመለከተ የታክስ መረጃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ መሳሪያዎቹ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኮምፒዩተርና የምህንድስና ትምርት ክፍል በኩል ፍተሻው እንዲከናወን በተደረሰው ስምምነት መሰረት እየታዩ በሚቀርበው ሪፖርት መሰረት ዕውቅና እንደሚሰጣቸው፣ በመመሪያው የብልሽት ጥገና አገልግሎት መሰጠት ያለበት በ48 ሰዓት ቢሆንም የዓመታዊ ምርመራ አገልግሎትን በሚመለከት የተቀመጠ ጊዜ ገደብ የሌለ መሆኑን፣ ነገር ግን በሁለቱም አገልግሎቶች በ48 ሰዓት ተጠግነው እንዲወጡ በአቅራቢዎቹ ባለሙያዎች በኩል ክትትል እንደሚደረግ፣ እስከ ሚያዚያ 2004 ባለው ጊዜ በአንዳንድ አቅራቢዎች መቶ በመቶ አገልግሎት የመስጠት ስራ መከናወኑን በአማካይ ሲታይ ደግሞ እስከ 94 በመቶ ደርሶ የነበረ መሆኑን እና በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው የሚወጡት 46 በመቶ ብቻ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

75. መሳሪያዎች ሲበላሹ በአፋጣኝ ተጠግነው አለመውጣታቸውና በየጊዜው መበላሸታቸው የግብይት መረጃ ተሟልቶ እንዳይያዝ እና በትክክለኛ መረጃ የተደገፈ የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥራ እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

የንግድ ፍቃድ የሚመልሱ ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚቋረጥበት ስርዓትን በተመለከተ

76. የንግድ ፈቃድ የሚመልሱ ግብር ከፋዮች ይጠቀሙበት የነበረው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አገልግሎት ከመስጠት የሚቋረጥበት እና በምን መልኩ መረጃውን ወጥቶ መያዝ እንዳለበት የሚያሳይ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ፡፡

77. የንግድ ፈቃድ የሚመልሱ የግብር ከፋዮች ይጠቀሙበት የነበረው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አገልግሎት ከመስጠት የሚቋረጥበት እና በምን መልኩ መረጃው ወጥቶ መያዝ እንዳለበት የሚያሳይ ሥርዓት ያልተዘረጋና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

78. ስለጉዳዩ የታክስ መረጃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የንግድ ፍቃድ የሚመልሱ ወይም የሚዘጉ እና በመዝጋት ሂደት ላይ ያሉ ግብር ከፋዩች የሚስተናገዱበት ስርዓት ተዘርግቶ ስራ ላይ መዋሉን፣ ሆኖም ግብር ከፋዩ መሣሪያውን በሚመለከት በራሱ ፍቃድ ለመሸጥ ወይም ለመውሰድ ለሚፈልግ የሚፈቀድበት ሁኔት ቢኖርም መሳሪያውን ሳይወስድ ቢቀር ምን መደረግ እንደሚገባ የሚገልፅ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱን ገልፀዋል፡፡

79. ፍቃድ የሚመልሱ ግብር ከፋዩች ሲጠቀሙበት የነበረውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አገልግሎቱ ሲያቋርጥ በምን መልኩ መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ስርዓት አለመዘርጋቱ መሳሪያው ለህግ ወጥ አገልግሎት እንዲውል በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

II **መረጃን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረግ ቅንጅታዊ አሰራርና የድጋፍና ክትትል ሂደቱ ዉጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡፡**

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች መረጃን በተገቢው መንገድ ስለመመዝገባቸው የሚያደረግውን ክትትል እና ቁጥጥርን በተመለከተ

80. ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሽያጭ መረጃ በተገቢው መንገድ መመዝገብአቸውን፣ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የተመዘገቡ መረጃዎች ወደ ባለስልጣኑ የመረጃ ቋት እየገቡ መሆኑን ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ፡፡

81. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተመዘገቡ የሽያጭ መረጃዎች ወደ መረጃ ቋት መተላለፍ አለመተላለፋቸው በየታክስ ማዕከሉም ሆነ በዋናው መ/ቤት ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የሚቻልበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ የሽያጭ መመዘግቢያ መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ መዋል ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2005 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ለግብር ከፋዩ ከተሸጡት 82141 የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎች ውስጥ 72964 (89%) አገልግሎት ላይ የዋሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 8755 (12%) ብቻ የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የሚያስተላልፉ ሲሆኑ፣ የተቀሩት 64209 (88%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሽያጭ መረጃን ወደ መረጃ ቋት የማያስተላልፉ መሆኑን፣ እና 5888 (12%) የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ከሲስተሙ ጋር ያልተያያዙ መሆናቸው በኦዲቱ ወቅቱ ታውቋል፡፡

82. የአማራ እና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ በሥራቸው ያሉ ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ክትትል የሚያደርጉ ቢሆንም መሳሪያዎቹ መረጃዎችን ወደ ዋናው ዳታ ቤዝ ማስተላለፍ አለማስተላለፋቸውን ግን ለማረጋገጥ በዋናው ዳታ ቤዝ የሚያዘውን መረጃ ለማየት ፓስ ወርድ ስላልተሰጣቸው ማረጋገጥ እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡

83. ይህንንም በተመለከተ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በቅድሚያ ትኩረት ሲሰጥ የነበረው መረጃ የሚልኩ መሳሪያዎች የሚጨምሩበትን ስርዓት ማጠናከር እንደነበር፣ አቅራቢዎች መሳሪያዎቹ እዛው ባሉበት ቦታ መረጃ መላካቸው የሚያረጋግጡበት ዌብ - ፖርታል እንዲዘጋጅ ከማድረግ ጀምሮ ሳይልኩ እንዳይወጣ የሚያደርግ አሰራር በመከተል ቢያንስ ለመጀመሪያ ጊዜ መረጃ ስለመላካቸው እያረጋገጠ እንደሚገኝ፣ ሆኖም የ(G*eneral* P*acket* R*adio* S*ervice*) (GPRS) ኔትወርክ ምልክት ወይም ሲግናል

በማይኖርበት ወቅት፣ ከኢትዮ ቴሌኮም ወደ መረጃ ቋት የሚያገናኝ መስመር ብልሽት ሲያጋጥም፤ የመረጃ ቋት (Server) ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ፤ የሽያጭ መረጃ ወደ መረጃ ቋት የማያስተላልፉ መሆኑን፤ በተጨማሪም የ(*General Packet Radio Service*) የ(GPRS) ኔትወርክ 40 በመቶ (40%) በአዲስ አበባ ስለማይሰራ በየጊዜው የሚያጋጥመውን የኔትወርክ መቆራረጥ ችግርን በተመለከተ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በተደጋጋሚ በመነጋገር ለመፍታት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ሊፈታ ያልቻለ ችግር መሆኑን፤ የተሸጠውና ሥራ ላይ የዋለው ልዩነት ደግሞ መሣሪያዎቹ አስፈላጊው ምዝገባ በቅጽ ተጠናቆላቸው በንግድ አድራሻቸው ተተክለው ግን የቅጹ መረጃ ወደሽያጭ አጠቃቀም ሶፍትዌር እንዲገባ ባለመደረጉ የተፈጠረ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በቀጣይነት ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከየታክስ ማዕከሉ መሳሪያዎቹ መረጃ መላካቸውን የሚከታተሉበት ስርዓት እንደሚመቻችና መረጃዎቹን በቀጥታ እንዲጠቀሙ የመግቢያ ፈቃድ (ፓስወርድ) እንደሚሰጣቸው፣ እስከ አሁን ግን የታክስ ማዕከላቱ የሽያጭ መረጃዎች የሚከታተሉበት ስርዓት የሌላቸው በመሆኑ መረጃ ሲጠይቁ በታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በኩል በሶፍት ኮፒ በማዘጋጀት ከመሳሪያዎቹ የተገኘ መረጃ እየተጠቀሰ ተጠናቅሮ እንደሚላክ ገልጸዋል፡፡

84. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሰበሰቡትን መረጃ ከጥቂቶቹ ይህውም ከ 12% በስተቀር ወደ ዋናው የባለስልጣኑ ዳታ ቤዝ አለማስተላለፋቸውና በባለሥልጣን መ/ቤቱም እያስተላለፉ ለመሆናቸው አለመረጋገጡ አገሪቱ ከታክስ ልታገኝ የሚገባትን ገቢ እንዳታገኝ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች መረጃ አያያዝን በተመለከተ

85. በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መለያ ቁጥር (TIN) ተሰጥቷቸው ተመዝግበው የንግድ ፍቃድ አውጥተው መክፈል የሚገባቸውን ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮችን ያሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት መረጃቸው ሊደራጅ እና ሊያዝ፣ በተያዘው መረጃ መሰረትም ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ሁኔታው እየተጣራ መክፈል የሚገባቸውን ግብር እንዲከፍሉ ሊደረግ እና የንግድ ስራቸውን ማቆማቸው ወይም መዝጋታቸው የተረጋገጠ ግብር ከፋዮችም የተመዘገቡበትን መለያቁጥር (TIN) በማስመለስ ፋይላቸው ከሲስተሙም ሆነ ከማህደር ሊዘጋ ይገባል፡፡

86. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ቅ/ጽቤቶች መክፈል የሚገባቸውን ግብር ያላሳወቁ 1506 ግብር ከፋዮች ያሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጅት መረጃቸውን በየግብር ዘመኑ አደራጅቶ በመያዝ ያለባቸው የግብር ዕዳ እንዲከፍሉ ለማስደረግ ክትትል እና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ሥራ

አቁመዋል ተብለው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፋይላቸው የተዘጉ ተብለው ከተያዙት 3362 ግብር ከፋዮች ውስጥ ሥራ እንዳቆሙ በማዕከል ደረጃ የሚታወቁት እና የተዘጉ ተብሎ በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) ላይ የሚታዩት 1504 ሲሆኑ ቀሪዎቹ 1858 ግብር ከፋዮች ግን በሥራ ላይ (active) እንደሆኑ የሚታይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

87. ስለጉዳዩ የቅ/ፅ/ቤቶች የድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ ተቀናጅቶ የመሥራት ክፍተት መኖሩ ግንዛቤ ተሰጥቶት ከፈቃድ ሰጪ አካላት ጋር በመግባባት በመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲፈጠር እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

88. ግብር ማሳወቅና እና መክፈል ያቆሙት ግብር ከፋዮች ተለይተው አለመታወቃቸው የግብር ግዴታቸውን የማይወጡ ግብር ከፋዮች እንዲበራከቱ እና መሰብሰብ የሚገባው ገቢ በአግባቡ እንዳይሰበሰብ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ የሚረዱ መረጃዎች ተጠናቅረው መያዛቸውን እና ጥቅም ላይ መዋላቸውን በተመለከተ

89. ለግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ የሚረዱ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተጠናቅረው በመረጃ ቋት /ዳታ ቤዝ/ ሊያዙ፣ የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ በመተንተንና በማጠናቀር ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለተጠቀሚዎች ሊሰራጭ፣ የተሰራጩት መረጃዎችም ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ለመከታተል እና ግብረ መልስ ለመሰብሰብ የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ፡፡

90. ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ መረጃዎች የሚያዙባቸው የተለያዩ የመረጃ ቋቶች በባለሥልጣን መ/ቤቱ ተደራጅተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መረጃ መስብሰቢያ፣ የጉምሩክ ስነሥርዓት ለገቢ ዕቃዎችም ሆነ ለወጪ ዕቃዎች የሚከናወንበት የአሲኩዳ ሲስተም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሲሰጥ የሚመዘገብበትና የአሻራ ምዝገባ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ሆኖም እነዚህ የመረጃ ቋቶች እርስ በርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface & Intranet) ተደርገው ያልተሰሩ መሆኑን፣ የተሰበሰበዉ መረጃ ተደራጅቶ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት የጥራት ደረጃውን ለመገምገምና ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ በተበታተኑ የመረጃ ቋቶች የተያዘው መረጃም ሆነ ከሶስተኛ ወገን በተለያየ ዘዴ የተሰበሰበው መረጃን የመሰብሰብና ተንትኖ የማጠናቀር እንዲሁም የማሰራጨት ተግባር ከዋናው መ/ቤት በስተቀር በቅ/ፅ/ቤቶችና በክልሎች እንደማይከናውን ታውቋል፡፡ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና

ክልሎች መረጃዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረገው ጥያቄ ሲቀርብ ብቻ መሆኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረጉ መረጃዎችም ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ክትትልና ግብረ መልስ የማይሰብሰብ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

91. ይህንንም በተመለከተ የምዕራብ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ተገልጋዩ የንግድ ፈቃዳቸውን ለመመለስና ንግድ ፈቃድ ለመወሰድ፣ ክሊራንስ ለመውሰድ የሚጠይቁ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ከዋናው መ/ቤት ሲጠይቁ መልስ የሚያገኙት ዘግይቶ በመሆኑ በሥራው ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ለታክስ ኦዲት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንደ የኢንዱስትሪ ግብዓት ቀመር እና ብክነተ ተረፈ ምርት የሚመለከቱ መረጃ ማግኘት አዳጋች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

92. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የገቢዎችና የጉምሩክ ባለሥልጣን የ(SIGTAS) እና የአሲኩዳ መረጃዎች እርስበርስ መያያዛቸውን (ኢንተርፌስ መፈጠሩን) ቢገልጽም ለክልሉ ግብር ከፋይ የሆኑ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ በአሲኩዳ እና በሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያዎችን ላይ የተያዙ መረጃዎችን መጠቀም አለመቻላቸውን፣ ክልሉን የሚመለከት የገቢ አስተዳደር መረጃዎችን ለመጠቀም ፓስወርድ ለመፍቀድና ለመከልከል የፌዴራሉ ፈቃድ ማስፈለጉን ለመጠቀም ሲጠይቁም አፋጣኝ ምላሽ የማያገኙ መሆኑን፣ የአማራ ክልል የገቢዎች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ደግሞ የሽያጭ መመዝገቢያና ሌሎች የዳታ መረጃዎችን አስተዳደር ለክልሎች አለመፈቀዱ ሥራቸው ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ እንደፈጠረባቸው ገልጸዋል፡፡

93. ይህን አስመልክቶ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በተጠናው የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ መሰረት የታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬትን የመረጃ ጥያቄ ሳይጠበቅ ለሁሉም ግብር ከፋዮች መረጃዎች ከተለያየ የመረጃ ሲስተም ተጠናቅረው እና ተተንትነዉ ለተጠቃሚዎች ወቅታዊ መረጃዎች እንዲደርሱ ማድረግ እንደሚገባ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉን፣ ይህንንም ስራ ለመጀመር እስአሁን ሶፍትዌር ባለመቀረጹ የቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ በወረቀት በማጠናቀርና በመተንተን መልስ በመስጠት ላይ እንደሚገኙ፣ ግብረ መልስ ለማግኘትም ማገናዘቢያ (check list) በማዘጋጀት መረጃዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም አዋጭ ሥርዓት ባለመሆኑ በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ አድርጎ ለመተግበር በዚህ በጀት ዓመት በዕቅድ መያዙን ገልጸዋል፡፡

94. የመረጃ ጥራትን መጠበቅ በተመለከተ እስካሁን መስፈርት ያልተዘጋጀለት እና በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ያልታየ በመሆኑ በቀጣይ በቡድን ደረጃ እንዲደራጅ የማሻሻያ ሃሳብ አቅርበው ለተቋሙ የአደረጃጀት ቡድን የቀረበ በመሆኑ የማሻሻያ ሀሳቡ ሲፈቀድ እና ቡድኑ ሲደራጅ በተዘገጀለት የስራ መዘርዝር መሰረት የአሰራር ስርዓት የሚዘጋጅ መሆኑን ገልፅዋል ፡፡

95. በተጨማሪም በመስሪያ ቤቱ ከተዘረጉ የመረጃ ቴክኖሎጂ መረቦች ውስጥ አጠናቅረው እና ተንትነው በየቅርንጫፍ መ/ቤቱ ለላኩት መረጃ ግብረ-መልስ ለማግኘት እንዲያስችላቸው በ(SIGTAS) የተወሰኑ ውሳኔዎችን የማየት ሥልጣን ያለው የመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ብቻ መሆኑን እንዲሁም ወደ መረጃ መረብ የገቡ የግዢ፣ የሽያጭ፣ የኢትዮጵያ የምርት ገበያ ድርጅት (ECX)፣ የወጪ መጋራት እና በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚተላለፉ መረጃዎችን በአዲስ አበባ የሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ክፍለ ከተሞችን ጨምሮ መጠቀም እንዲችሉ ሰልጥነው ማሰልጠን ለሚችሉ የኦዲት እና የአወሳሰን ሰራተኞች ስልጠና የሰጡ ቢሆንም ክፍለ ከተሞች የይለፍ ቃል ስላልተሰጣቸው መጠቀም እንዳልጀመሩ ገልጸዋል፡፡

96. የግብር ከፋዮችን የሥራ እንቅስቃሴ አስመልክቶ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በተቀናጀ መልክ ለግብር አወሳሰን በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ መሰብሰብ የሚገባው የታክስ ሂሳብ እንዳይሰበሰብ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

የመረጃ አቅርቦት መስጫ ማዕከል መኖሩን በተመለከተ

97. የመረጃ መስጫ ማዕከላትን በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ በመክፈት ለግብር ከፋዩ ወይም ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ተገቢው ማብራሪያ ሊሰጥ ይገባል፡፡

98. በኦዲቱ ወቅት የመረጃ መስጫ ማዕከላት በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ያልተቋቋሙ በመሆኑ ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ የማይሰጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

99. ስለጉዳዩ የደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመረጃ አቅርቦትና ማብራሪያ አገልግሎት በቅ/ጽ/ቤቶች በአደረጃጀት ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ በቀጣይ በሚደረገው የአደረጃጀት ክለሳ ላይ እንዲታይ ጥያቄ መቅረቡን፣ በዋናው መ/ቤት ግን በደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የታክስ እና የጉምሩክ መረጃና ማብራሪያ ቡድን መረጃዎችን በጽሁፍ፣ በአካል እንዲሁም በስልክ የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

100. የመረጃ መስጫ ማዕከላት በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ተቋቁሞ ለግብር ከፋዩ (ለተገልጋዩ) በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ ባለመሰጠቱ ግብር ከፋዩ የሚፈልገዉን መረጃ በተሟላ መልኩ እንዳያገኝ እና ለአላስፈልጊ ወጪና የጊዜ ብክነት እንዲዳረግ አድርጎታል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያዎች

101. የግብር መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና የአስተዳደር ስርዓት የተጣጣመ ወጥ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥን በተመለከተ

- ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የገቢ አሰባሰብና የታክስ አወሳሰን ሂደት በጥራትና በተቀላጠፈ መልኩ እንዲከናወን ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የግብር ከፋዩን መረጃ በተሟላ ሁኔታ አደራጅቶ ያልያዘ መሆኑ፣
- ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የተሰጣቸው ግብር ከፋዩች መኖራቸው፣
- በባለሥልጣኑ በግብር ከፋይነት የተመዘገቡ ግብር ከፋዮች በየጊዜው ግብር መክፈላቸው ወይንም ሥራ ማቋረጣቸው እየተረጋገጠ መረጃቸው ወቅታዊ የማይደረግ መሆኑ፣
- የግብር መክፈያ ጣቢያቸው የማይታወቁ ግብር ከፋዮች መኖራቸው፣
- ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት/ ጣቢያ ሲቀይሩ በሰነድና በ(SIGTAS) ያለው መረጃ ወደ ተዛወሩበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት/ ሙሉ ለሙሉ መዛወሩ የማይረጋገጥ መሆኑ፣
- በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላት በማህደር (Hard copy) የተያዘው የግብር ከፋይ መረጃ እና በመንግስት የታክስ አስተዳደር ሥርዓት (SIGTAS) ተመዝግበው የተያዙ መረጃዎች የማይናበቡ መሆኑ፣
- ለግብር አወሳሰንና አሰባበሰብ የሚያስፈልጉ የግብር ከፋዮች የግዢ እና የሽያጭ (የግብይት መረጃዎች) እና የ3ኛ ወገን መረጃዎች በተሟላ መልክ የማይሰበሰቡ፣ የተሰበሰቡትም በተሟላ ሁኔታ በማዕከል ደረጃ ወደ ተቋቋመው የመረጃ ቋት ተጠቃለው ያልገቡ መሆኑ፣
- በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የግብር ከፋዮች ሀብትና ንብረት ተመዝግቦ የሚያዝበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- የግብር ከፋዮች መረጃ ለውሳኔም ሆነ ለሌሎች ተጠቃሚዎች በሚያመች መልኩ እንደ የሥራ መስኩ እና ዓይነት እየተለዩ (ለምሳሌ በግብርና ዘርፍ፣ በኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪ ዘርፎች ወዘተ--) ተደራጅተው ያልተያዙ መሆኑ፣

- ግብር ከፋዮች የአቀረቡአቸውን ቅሬታና አቤቱታዎች፣ የተሰጡ ውሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃችን የሚገልጹ መረጃዎች በተደራጀ ሁኔታ ተጠናቅረው የማይያዙ መሆኑ፣
- ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አሰረጫጨት ፖሊሲ ተቀርጾ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- አገር አቀፍ የመረጃ ልውውጥ እና የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር እንዲኖር በፌደራል፤ በክልል መንግስታት እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል የመግባቢያ ሰነድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- በደንቡ መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን ከሚገባቸው ግብር ከፋዮች ውስጥ መሳሪያውን የማይጠቀሙ መኖራቸው፣
- ባለስልጣን መ/ቤቱ እውቅና ባልሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሶፍትዌር የሚጠቀሙ ግብር ከፋዮች መኖራቸው፣
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ሲበላሹ በተበላሹ በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሥራ ላይ የማይውሉ መሆኑ፣

102. መረጃን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረግ ቅንጅታዊ አሰራርና የድጋፍና ክትትል ሂደቱ ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፡፡

- ለግብር ከፋዩ ከተሸጡት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ውስጥ 88% የሽያጭ መረጃን ወደ ባለስልጣን መ/ቤቱ የመረጃ ቋት የማያስተላልፉ መሆኑ እና ባለስልጣን መ/ቤቱ ክትትል እና ቁጥጥር የማያደርግ መሆኑ፣
- ለባለስልጣን መ/ቤቱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት እየሰሩ ለመሆኑ ክትትል እና ቁጥጥር የማይደረግ እና ግዴታቸውን ባልተወጡ አቅራቢዎች ላይ ህጋዊ እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች ያሉበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ያላባቸውን የግብር ዕዳ እንዲከፍሉ ክትትልና ቁጥጥር ያልተደረገ መሆኑ፣
- የንግድ ስራቸውን ማቆማቸው ወይም መዝጋታቸው የተረጋገጠ ግብር ከፋዮችም የተመዘገቡበትን የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN) በማስመለስ ፋይላቸው ከሲስተምም ሆነ ከማህደር እንዲዘጋ የማይደረግ መሆኑን፣
- ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ የሚሰጥ ክፍል በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አለመኖሩ፣

➢ ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ በባለሥልጣኑ የተደራጁ የተለያዩ የመረጃ ቋቶች (የመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መረጃ መሰብሰቢያ፣ የጉምሩክ ስነሥርዓት ለገቢ ዕቃዎችም ሆነ ለወጪ ዕቃዎች የሚከናወንበት የአሲኩዳ ሲስተም፣ የግብር ከፋይ የአሻራ ምዝገባ) ውስጥ የተያዘው መረጃ እርስ በእርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface) ያልተደረጉ መሆኑን፣

➢ ለግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ የሚረዱ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ በመተንተንና በማጠናቀር ጥቅም ላይ እንዲውል ለተጠቃሚዎች በተገቢው መንገድ እየተሰራጩ አለመሆኑ እና የተሰራጩ መረጃዎች ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ለመከታተል እና ግብረ- መልስ ለመሰብሰብ የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

103. በአጠቃላይ ከላይ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች እና ግድፈቶች በባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚከናወነው የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት፣ እና አስተዳደር ስርዓት ጊዜ እና ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለው እና ውጤታማ እንዳይሆን እና ባለስልጣን መ/ቤቱ የተቋቋመበትን ዓለማ በአግባቡ እንዳያሳካ እንቅፋት ይሆናሉ፡፡ ስለሆነም በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል ከላይ የተመለከቱትን የአሰራር ክፍተቶች እና ግድፈቶች ለማስወገድ ወይም ለማሻሻል ይረዳሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

103. የግብር መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና የአስተዳደር ስርዓት የተጣጣመ ወጥ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን ማረጋገጥን በተመለከተ

- ❖ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የግብር አወሳሰንና አሰባሰብን ለማቀላጠፍ የዘረጋውን የመረጃ ቴክኖሎጂ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የግብር ከፋዩን መረጃ በአግባቡ ሊያደራጅ እና ከፍተኛ ወጪ ወጥቶበት ሥራ ላይ የዋለውን የታክስ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አስተዳደር ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ለተግባራዊነቱም ስራውን ለሚያከናውኑ ባለሙያዎች አስፈላጊውን ስልጠና በመስጠት መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ መሰብሰብ ይጠበቅበታል፡፡
- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሥሩ ያሉትን ግብር ከፋዮች መረጃ በየደረጃው በአግባቡ መመዝገቡ፣ ሊያጣራ እና አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አለመሰጠቱን ሊቆጣጠርና ከአንድ በላይ የግብር መለያ ቁጥር የተሰጣቸውን በማጣራት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡
- ❖ ግብር ከፋዮች ግብር ለመክፈል በተመዘገቡበት የግብር መክፈያ ጣቢያ መክፈል የሚገባቸውን ግብር መክፈላቸውን ሊያረጋግጥ፣ ሥራ አቋርጠው ከሆነም ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማቋረጣቸውን በማረጋገጥ መረጃው ወቅታዊ መድረግ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ግብር ከፋዮች ግብር የሚከፍሉበትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ ሲቀይሩ በሰነድ ያለው መረጃ ሙሉ በሙሉ ወደ ቀየሩት የግብር መክፈያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ጣቢያ መዘዋወሩን በየጊዜው ሊያረጋግጥና በSIGTAS ያለው መረጃ ወደ ተዛወሩበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲዛወር ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ በማህደር (Hard copy) የተያዙት መረጃዎች እና በ SIGTAS የተያዙ መረጃዎች ተመሳሳይ እንዲሆኑ እና እንዲናበቡ የማጥራት ሥራ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ተከናውኖ መረጃዎቹ ተመሳሳይ መሆናቸው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሊያረጋግጥ እና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግብር ከፋዮችን የግብይት (የግዢ እና የሽያጭ) መረጃዎች እና የ3ኛ ወገን መረጃዎች በተሟላ መልክ ሰብስቦ በመረጃ ቋት በመያዝ፣ በማጥራት፣ በመተንተንና የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ይጠበቅበታል፡፡
- በባለሥልጣን መ/ቤቱ እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግብር ከፋዮች በግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ጋር በተያያዘ በየደረጃው የሚያቀርቡአቸው ቅሬታዎችና አቤቱታዎች፣ የተሰጡ ውሳኔዎችና የተወሰዱ እርምጃችን የሚገልጹ መረጃዎች በዝርዝር ተደራጅተው የሚያዙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ወጥ የሆነ ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አሰረጫጨት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ ከታክስ ጋር የተያያዘ የመረጃ ልውውጥ እና የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ በፌደራል፣ በክልል መንግስታት እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል የመግባቢያ ሰነድ በሁሉም በሚመለከታቸው አካላት ተፈርሞ ሥራ ላይ እንዲውል ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው ግብር ከፋዮች በሙሉ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ፣ በየደረጃው ተፈጻሚ ለመሆኑ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ የሆኑ ግብር ከፋዮች የሚጠቀሙት ሶፍት ዌር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚጠቀምበት የቴክኖሎጂ ሥርዓት ጋር የሚጣጣምና የሚናበብ፣ ለሁሉም የሥራ ዘርፍ የሚያገለግሉ እና ተስማሚ ሆነው ሊዘጋጁ፣ ከዚህ በፊት ሥራ ላይ የዋሉት ሶፍት ዌሮች ያለባቸው ችግር እየተፈተሸ ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ዕውቅና ባልተሰጠው ሶፍትዌር የሚጠቀሙ ግብር ከፋዮች ላይ ተገቢው ክትትል እየተደረገ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡
- የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ሲበላሹ በተበላሹ በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረግ እንዲሁም በስራ ላይ እያሉ በየዓመቱ እድሳት የሚደረግበት ሁኔታ ከአቅራቢዎች ጋር በመመካከር መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

104. መረጃን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረግ ቅንጅታዊ አሰራርና የድጋፍና ክትትል ሂደቱ ዉጤታማ መሆኑን በተመለከተ

- በባለሥልጣን መ/ቤቱ በቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች በክልሎች እና የከተማ መስተዳደሮች ግብር ከፋዮች በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የሚመዘገቡት የሽያጭ መረጃ ወደ

ባለስልጣን መ/ቤቱ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት በትክክል መግባቱን ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ፣ በየደረጃው ያሉት ግብር ሰብሳቢ አካላት ተግባራዊነቱን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር የሚችሉበትን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

- ❖ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት አሟልተው እና ስምምነት ፈርመው በገቡት ውል መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ በማያቀርቡት እና ተገቢውን የጥገና ሥራ በማያከናውኑ አቅራቢዎች ላይ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ግዴታቸውን በማይወጡ አቅራቢዎች ላይም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ይኖርበትል፡፡
- ❖ በባለስልጣን መ/ቤቱ ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች መለያ ቁጥር (TIN) ተሰቷቸው ተመዝግበው እና የንግድ ፍቃድ አውጥተው የሚገባቸውን ግብር ማሳወቅ እና መክፈል ያቆሙ ግብር ከፋዮች በሚመለከት በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተያዘው መረጃና በዋናው መ/ቤት የተያዘው መረጃ ተመሳሳይ እንዲሆን የማጥራት ስራ ተከናውኖ መክፈል የሚገባቸውን ግብር እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ የንግድ ስራቸውን ማቆማቸው ወይም መዝጋታቸው የተረጋገጠ ግብር ከፋዮች የተመዘገቡበት መለያ ቁጥር (TIN) ተመልሶ ፋይላቸው ከሲስተምም ሆነ ከማህደር እንዲዘጋ መደረጉን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡
- ❖ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተደራጁ ለግብር አሰባሰብና አወሳሰን የሚረዱ የተለያዩ የመረጃ ቋቶች (የመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት (SIGTAS)፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መረጃ መስብሰቢያ፣ የጉምሩክ ስነሥርዓት ለገቢ ዕቃዎም ሆነ ለወጪ ዕቃዎች የሚከናወንበት የአሲኩዳ ሲስተም፣ የግብር ከፋይ የአሻራ ምዝገባ) ውስጥ የተያዙት መረጃዎች እርስ በእርሳቸው እንዲመጋገቡና እንዲናበቡ (Interface) በማደረግ ለግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ መረጃውንም በግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ እንዲሁም ታክስ ኦዲት ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች በአግባቡ የሚጠቀሙበት መንገድ ባለሥልጣኑ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ❖ ባለስልጣን መ/ቤቱ ለግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ የሚረዱ ግብር ከፋዮችን የሚመለከቱ መረጃዎች የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ በመተንትንና በማጠናቀር ጥቅም ላይ እንዲውል ለተጠቀሚዎች በተገቢው መንገድ መሰራጪታቸውን፣ እና መረጃዎችም ጥቅም ላይ መዋላቸው ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ግብረ- መልስ መሰብሰቢያ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ግብር ከፋዮችም ሆኑ ሌሎች ተገልጋዮች ለሚፈልጉቸው ማብራሪያዎችም ሆነ ጥያቄዎች በቀላሉ መረጃና ምላሽ የሚያገኙባቸው ዴስኮች ወይም እንደ አስፈላጊነቱ የመረጃ መስጫ ማዕከላትን በየቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ በማቋቋም ለግብር ከፋዩ ወይም ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ እንዲሰጥ አስፈላገውን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት ፡፡

105. በአጠቃላይ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የግብር መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት እና አስተዳደር ስርዓት የተጣጣመ ወጥ እና ውጤታማ እንዲሆን ሊያደርግ፣ የሚሰበሰበውም መረጃ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋሉን መከታተል የሚያስችል ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ እና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እና ለክልሎች የሚያደርገውን የድጋፍና ክትትል ሂደትን በማጠናከር በአዋጅ የተሰጠውን ግዴታ መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ በናሙና የታዩት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹና በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የክልል መስተዳደር አካላት ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/
የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና የአስተዳደር ስርዓት በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ወጪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ላመደራጀትና ለመለዋወጥ በሚያስችል እና ዉጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገምን	1. ልማትን የሚደግፍ ዘመናዊ የታክስ መረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	2. የግብር መረጃ አሰባሰብ፤ አደረጃጀት እና አስተዳደሩ አገራዊ፣ ወጥ እና ተመጋጋቢነት ያለው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	3. የግገር፤ የሽያጭና ግብይት መረጃዎችን (፤ከሁሉም ግብር ከፋዮች ፤ ከ 3ኛ ወገን እና ከመረጃ ሰጪዎች) ተሰብስቦ በአግባቡ ሊደራጁ ይገባል፡፡
	4. በባለሥልጣን መ/ቤቱ የታክስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓትን በተመለከተ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	5. በፌደራል ፤በክልል መንግስታት እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል ወጥነት ያለዉ የታክስ መረጃና የልምድ ልዉዉጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ሊኖር ይገባል፡፡
	6. ከሁሉም ግብር ከፋዮች ፤ ከ 3ኛ ወገን እና ከመረጃ ሰጪዎች ተሰበስቦ የተደራጀዉ መረጃ በአግባቡ በመረጃ ማዕከል /ቋት/ ሊያዝ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የተቋሙ ስትራቴጂክ ፕላን(2003-2007)
	7. ለታክስ ውሳኔ የሚረዳ መረጃ እንዲኖር የሁሉም ግብር ከፋዩ ሃብትና ንብረት ተመዝግቦ የሚያዝበተን ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡-የተቋሙ ስትራቴጂክ ፕላን(2003-2007)
	8. በመረጃ ዳታ ቤዝ /ቋት/ተደራጅቶ የተያዘዉ መረጃ ተገምግሞ ወቅታዊ ሊሆን ይገባል፡፡
	9. በመረጃ ዳታ ቤዝ /ቋት/ተደራጅቶ የተያዘዉ መረጃ የተገልጋይን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ በመተንተንና በማጠናቀር በመረጃ መረቡ ላይ ሊካተቱ ይገባል፡፡
	10.ከመረጃ ሰጪ አካላት ጋር ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥን ለማሳደግ በጥናት የተደገፈ የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
	11. 24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጥ ከተለያዩ አካላት መረጃ ለመቀበል የሚያስችል የጥሪ ማዕከል (Call center) ሊቋቋምና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	12.ሁሉንም መረጃዎች ያማከለ ወጥ የመረጃ መሰብሰቢያ ፎርማትና የተሟላ ዳታቤዝ መቅረጽና ለመረጃ ተጠቃሚው ምቹ ሊደረግ ይገባል፡፡
	13. ወጥ የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት፣ ሁሉንም ግብር ከፋዮች የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል፡፡
	14. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ መሣሪያዎች በተበላሹ በ48 ሰዓት ውስጥ የጥገና አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡
	15. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ያለውን የመረጃ ፍሰትና ጥራት ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት መኖር አለበት፡፡
	16. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አቅራቢዎች አለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ማቅረባቸዉ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	17. የንግድ ፈቃድ የሚመልሱ የግብር ከፋዮች ይጠቀሙበት የነበረው

	የሽያጭ መመዝግቢያ መሳሪያ አጠቃቀም የሚቋረጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	18. ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት ግብር ከፋይ በጣት አሻራ ላይ የተመሰረተ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሊኖረዉ ይገባል፡፡
	19. የጣት አሻራ በመስጠት የተመዘገበ ግብር ከፋይ የግብር ከፋይ መለያ መታወቂያ ሊሰጠዉ ይገባል፡፡
	20. የመረጃ አቅርቦትና ቅብብሎሽ ሂደቱን ለማቀላጠፍ በሚደግፍ መልኩ በተቋሙ የሚተገበሩ ደንቦችና መመሪያዎች ተደራጅተዉ ሊያዙና ለሚመለከተዉ አካል ሊሰራጭ ይገባል ፡፡
2. መረጃን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ቅንጅታዊ አሰራርና የድጋፍና ክትትል ሥርዓትየተዘረጋ መሆኑንና ሂደቱ ዉጤታማ መሆኑን መገምገም በተመለከተ፡፡	21. የታክስና ጉሙርክ፤ የገቢና ወጪ፤ የአምራችና አከፋፋዮች እንዲሁም የዋጋና የሶስተኛ ወገን የሽያጭ መረጃዎች ወቅታዊ በሆነናለግብር አወሳሰን በሚጠቅም መልኩ ተደራጅቶ ለሚመለከተዉ አካል ሊሰራጭ ይገባል፡፡
	22. ከሁሉም ግብር ከፋዮች ከ 3ኛ ወገን እና ከመረጃ ሰጪዎች ተሰበስቦ የተደራጀዉ መረጃ በአግባቡ ተጠብቆ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የመረጃ ደህንነት ፖሊሲ ሊኖር ይገባል፡፡
	23. የተሰበሰበዉ መረጃ ተደራጅቶ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት የጥራት ደረጃውን መገምገምና ለማረጋገጥ የሚያስችል መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡
	24. ለግብር አወሳሰን ጥቅም ላይ እንዲዉሉ የተሰራጩ መረጃዎችን ጥቅም ላይ ስለመዋላቸዉ ለመከታተል እና ግበረ-መልስ ለመሰብሰብ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
	25. የመረጃ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም ለተገልጋዩ በቂ የመረጃ አቅርቦት እና ማብራሪያ መስጠት ይኖርበታል፡፡
	26. በፌደራል ፤በክልል መንግስታት እና በከተማ መስተዳድሮች መካከል ወጥነት ያለዉ የታክስ መረጃና የልምድ ልዉዉጥ ለማድረግ የሚያስችል የስምምነት ሰነድ ሊኖር ይገባል፡፡

አባሪ 2

የባለሥልጣኑ ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 3

የሽያጭ መ/መ/መሳሪያ አቅራቢዎች ከሸጡት ውስጥ በአማካይ በዓመት ለጥገና የቀረቡ እና ተጠግነው የወጡትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

ተ.ቁ	የሽጭ መ/መ/መሳያ አቅራቢ ስም	እስከ 2005 የተሸጠው ብዛት	በአማካይ በአመት ወደ ጥገና የሚገቡ	በ48 ሰዓት ውስጥ ተጠግነው የሚወጡ	በ48 ሰዓት ውስጥ ጥገና ያላገኙ	በ48 ሰዓት ውስጥ ጥገና ያላገኙ በመቶኛ
1	ፔተራም ኃ/የተየግ /ማ	7857	2387	986	1401	59%
2	ኦሜዳድ ኃ/የተየግ/ማ	30604	795	478	317	40%
3	ሓሮን ኮ ምፒውተር ኃ/የተየግ /ማ	22106	1213	617	596	49%
4	ጁፒተር የንግድ ስራ ድርጅት	5565	3186	2064	1122	35%
5	ጅናአድ	7435	1983	10101	882	44%
6	አዲስ ሆም ዲፓኃ/የተየግ /ማ	5885	1171	228	943	80%
7	አይፖስ ኢንተረናሽናል	6891	1784	723	1061	59%
8	አምባሰል የንግድ ኃ/የተየግ /ማ ስራዎች	15100	2324	653	1671	72%
9	ቢፍቱ አዱኛ ቢዝነስ ኢ.ማ	3023	492	236	256	52%
10	ፔይመንት ቢዝነስ ሶሉሽን	2912	129	60	69	53%
11	ቤድፋም ኢንተርናሽናል ኃ/	1763	3	1	2	67%
	ድምር	82141	15467	7147	8320	54%